የእግዚአብሄር ልጅ ስለሆኑ ደስ ይበልዎት!!

መላዕክትም እኛም ደስ ብሎናል!! እግዚአብሔር ይመስገን።

<u>ከውሳኔ በኃላ ምን ማድረግ ይገባል?</u>

1. <u>የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ።</u> ለሰውነታችን/ለሥጋችን/ምግብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ በመንፈስ ለማደግ እንደዚሁ የእግዚአብሄር ቃል ያስፈልገናል።በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ህጻናት ተንኮል የሌለበትን የቃሉን ወተት ተመኙ (1ኛጴጥ2፥2)

2. <u>በጸሎት መትጋት።</u>ለክርስትና ሕይወት ጸሎት በጣም አስፈላጊ ነው።የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊሰጠን የሚችል ጌታ አለን።ፊሊ4፥19 ልጅ ስለሆንክ የመጠየቅ መብት አለህ።ኤፌ3፥20ለምኑ ይሰታችኃል ፈልጉ ታገኙማላችሁማቴ7፥7የሚለው ተስፋ ላንተም ነው።

4. <u>ጌታ ያረገልህን መስክር።</u>ጌታ ያደረገልህን የእምነትና የህይወት ለውጥ ለሌሎች መስክር።አንተ የቀመስከውን አዲስ ህይወት እንዲቀምሱ ጋብዛቸው።"እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክርነታቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም ራዕ12፥11" የሱስ ጌታ ነው ብለህ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሄርም ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ ።ሮሜ10፥9

5. <u>ከክርስቲያኖች ጋር ህብረት አድርግ።</u> ዛሬ በመንፈሳዊ ህይወትህ እንደገና በመወለድህ አዲስ ቤተሰብ መስርተሃል"በክርስቶስ የሱስ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁ።ገላ3፥26"ስለሚል የክርስቲያኖችን ህብረት ለመንፈሳዊ እድገት ይጠቅምሃል።" ወንድሞች በህብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው እነሆም ያማረ ነው።መዝ133፥1

የበለጠ የእግዚአብሄርን ቃል ለመማር ወይም ጥያቄ ከአልዎት ከዚህ በታች ባለው አድራሻ ምን ጊዜም ሊያገኙን ይችላሉ።



## የክርስቶስ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን

## Evangelische Christus Gemeinde


Evangelische Christus Gemeinde
Rudolf-Diesel Straße-9, 85221 Dachau
www.cecinmunich.org
E-Mail:cecinmunich@yahoo.com
Tel:017684852691
Evangelisation Dienst:017645613900


Gottesdienst:So:11:00-13:00Uhr
Bibelkreis:So:10:00-11:00Uhr
Gebetsstunde:Sa:15:00-18:30Uhr

„እግዚአብሔር ይባርኮዎት "

# የደህንነት ውሳኔ አድርግ



<u>ኃጢአት ምንድር ነው?</u>

- ኃጢአት ዓመፅ ማለት ነው።"ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል ኃጢአትም ዓምፅ ነው።"1ኛዮሓ3፥4
- ኃጢአት ማንኛውም ከእግዚአብሔር ክብር የሚያጎድለንን ነገር ማድረግ ማለት ነው።" ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤"ሮሜ 3፥23
- ኃጢአት አንድን ነገር ትክክል አለመሆኑን እያወቅን ነገር ግን በአመጽ የምናደርገው ነገር ማለት ነው። "ዓመፅ ሁሉ ኀጢአት ነው።"1ዮሓ5፥17
- ኃጢአት መልካምን ነገር ማድረግ እንዳለብን እያወቅን ነገር ግን ሳናደርግ የምንተወው ማለት ነው።"እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሰራው ኃጢአት ነው።"ያዕቆብ4፥17

## የደህንነት መንገድ

# የደህንነት:ውሳኔ:አድርግ

- ኃጢአት ከሰው የሚወጣና ሰውን የሚያረክስ ማለት ነው ።“እርሱም አለ፦ ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው።ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል።”ማር7፥20-23

2. <u>ኃጢአት ወደ ዓለም እንዴት ገባ?</u>

- አዳምና ሄዋን በገነት ሳሉ እግዚአብሔር አትብሉ ካላቸው ከዛፍ ፍሬ በሰይጣን ተታልለው በመብላታቸውና የእግዚአብሄር ትዕዛዝ ባለመጠበቃቸው የተነሳ የሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአተኞች ሆኘዋል.።ዘፍ3፥1-6
- ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ ።ሮሜ5:12
- “የለምየሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ።ሁሉ ዐመፀ በአንድነትም ረከሱ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም አንድም ስንኳ የለም።”መዝ14:2-3
- “ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥.....ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል። “

  ሮሜ3:10-23

የደህንነት :ውሳኔ :አድርግ

3. <u>የኃጢአት ዋጋ ምንድር ነው?</u>

- ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው ዕብ 9:27
- እነዚያም(ኃጢአተኞች) ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።ማቴ25:46
- የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው።ሞት ስንል በሥጋ አንድ ጊዜ የምንሞተው ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ ሞት ነው።ሮሜ 6:23

4. <u>ከዘላለም ፍርድ/ሞት/እንዴት መዳን ይቻላል?</u>

- መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።ሐዋ4፥12 እርሱም የሱስ ነው።ከዘላለም ሞት ለመዳን አንድና ብቸኛ መንገድ የሱስ ነው።ጽድቃችሁ የሱስ ክርስቶስ ነውና።
- ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ  በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።ዮሐ4፥6
- የሱስ............ እንዲህ አለ።ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ ።በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል።ዮሐ7፥37-38
- ደግሞም የሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።ዮሐ8፥12
- እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደባችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም እረፍት እሰጣችኃለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።ማቴ11፥28-30
- የሱስም አለ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።ዮሐ5፥24

የደህንነት:ውሳኔ :አድርግ

- በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።ዮሐ3፥16

5 <u>የዘላለም ህይወት ለማግኘት ምን ማድረግ ያስፈልጋል?</u>

- <u>ኃጢአተኝነታችንን መቀበል</u> ።ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሓስተኛ እናደርጋዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።1ኛ ዮሓ 1፥10
- <u>ኃጢአትን መናዘዝ።</u> እውነተኛ ለውጥ ለማግኘት ግልጽና ንጹህ እንዲሁም ከልብ የመነጨ ኑዛዜ ያስፈልጋል።ንስሃ መግባት ማለት “ጌታ ሆይ ኀጢአተኛ ነኝ ይቅር በለኝ “ብሎ ከእውነተኛ ልብ መጠይቅ ማለት ነው።ከንስሓ በፊት ደህንነት የለም።”በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ፃድቅ ነው።1ኛ ዮሓ1፥9
- <u>ውሣኔ አድርግ።</u> የዘላለም ህይወት ለማግኘት ከክርስቶስ የሱስ ሌላ መዳኛ እንደሌለ በልብህ አምነህ እንደግል አድኝና ጌታህ አድርገህ በመቀበል መወሰን ያስፈልጋል ።”ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሄር ልጆች እንዲሆኑ ስልጣንን ሰጣቸው።ዮሓ1፥12
- <u>የንስሃ ፀሎት ማድረግ።</u> ከላይ ያነበቡትን ሃሳብ እውነትነቱን ካውቁና ከወሰኑ ከዚህ የሚከተለውን የንስሃ ጸሎት በእምነትና በእውነት ከልብዎ ይጸልዩ።

<u>ጌታ ሆይ ቃልህ እንደሚለው ኃጢያተኛ መሆኔን አምናለሁ። በሰራሁትም መልካም ሥራም እንደማልድን ተረድቻለሁ። ስለዚህ በዚህች ደቂቃ ኃጢአተኛ መሆኔን አምኜ በፊትህ ከልቤ ንስሃ እገባለሁ።በአዳም በኩል የተላለፈውንና ያደረኩትን ኃጢአት ይቅር በለኝ።ጌታ የሱስ ሆይ እኔን ለማዳን ከአብ ዘንድ መጥተህ የመስቀል ሞት ስለሞትክልኝ አመሰግናለሁ።ጌታየን እንደግል አዳኜና መዳሓኒቴ አድርጌ እቀበልሃለሁ።ከአሁን ሰዓት ጀምሮ የህይወቴ ገዥ እንድትሆን እለምንሃለሁ። ሕይወቴን  ሙሉ በሙሉ ለአንተ እሰጣለሁ።ኃጢአቴንም ይቅር ስላልከኝ አመሰግናለሁ።አሜን!!</u>